

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ

ውልደቱ እና እድገቱ

- በገሊላ ባህር አጠገብ በምትገኘው ቤተሳይዳ ተወለደ።
- የዮና ልጅ ስምዖን ጴጥሮስ (ኬፋ)
- የስሙ ትርጓሜ ‘አለት ፣ መሰረት’ ማለት ነው።



ማቴዎስ 16 ፡ 13−18

13 ኢየሱስም ወደ ፊልጶስ ቂሣርያ አገር በደረሰ ጊዜ ደቀ
መዛሙርቱን ፦ ሰዎች የሰውን ልጅ ማን እንደ ሆነ ይሉታል? ብሎ
ጠየቀ።

14 እነርሱም፦ አንዳንዱ መጥምቁ ዮሐንስ፥ ሌሎችም ኤልያስ ፥
ሌሎችም ኤርምያስ ወይም ከነቢያት አንዱ ነው ይላሉ አሉት።

15 እርሱም፦ እናንተስ እኔን ማን እንደ ሆንሁ ትላላችሁ?
አላቸው።

16 ስምዖን ጴጥሮስም መልሶ ፦ አንተ ክርስቶስ የሕያው
እግዚአብሔር ልጅ ነህ አለ።

17 ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፦ የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥
በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና
ብፁዕ ነህ።

18 እኔም እልሃለሁ ፥ አንተ ጴጥሮስ ነህ፥ በዚችም ዓለት ላይ
ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ ፥ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም።



ሐአገልግሎት መጠሁት

- በወንድሙ እንድርያስ አማካኝነት
- ወደ ጌታችን የቀረበውና ከአሣ አጥማጅነት ወደ ነፍሳት ማጥመድ ሐዋርያዊ አገልግሎት
- የተጠራው በ55 ዓመት እድሜው ነበር
- ለንስሐ እና መዐርገ ክህነት በልዩነት ተምሳሌት ነው



ሀገረ ስብከቱ

† ‘‘ቅዱስ ጴጥሮስ

- በፍልስጤም
- በሶርያ
- በጳንጦን
- በገላትያ
- በቀጰዶቅያ
- በቢታንያ
- በኋላም ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር በሮሜ ሰብኳል ።

† ምንም የርሱ ክፍል ሮም ብትሆንም አርድእትን ስለ ምጽናት በሁሉም አሕገራት ዙሯል።

የቅዱስ ጴጥሮስ መጠሪያዎች

- ሊቀ ሐዋርያት
- ሊቀ ሮሎት (የእረኞች / ሐዋርያት አለቃ)
- መሠረተ ቤተ ክርስቲያን
- ኰኩሐ ሣይማኖት (የሣይማኖት ዐለት)
- አርሳይሮስ (የዓለም ሁሉ ፓትርያርክ)

የቅዱስ ጴጥሮስ መጻሕፍት



የጻፈው መልዕክት

† የመጀመርያ

በቅዱስ እስጢፋኖስ ሰማዕትነት ተሳቀው ለተሰደዱ የአይሁድ ክርስቲያኖች ማጽናኛ ይሆን ዘነድ።

† የሁለተኛው

በአዋጅ ታስሮ በነበረበት ወቅት ምእመናንን በምንፍቅና ትምህርቶች አውከዋቸው ነበርና ለጥያቄዎቻቸው መልስ ይሆኑ ዘንድ ጽፏል።


አብኑት

† አስቀድሞ "አልታጠብም" በሚል ተከራክሮ የነበረ ቅዱስ ጴጥሮስ (ፈጣሪነቱን ቢያስብ÷ ትህትናው ቢበዛበት) እሺ ብሎ ታጥቧል። ኋላም "ካልቀረስ እኔም ልጠብህ" ብሎ ጌታን ለምኖታል።

† ጌታም "እሺ" ብሎ ታጥቦለታል። ይህም ለቅዱስ ጴጥሮስ የክብር ክብር ሆኖለታል። (ለመኑ ተውህበ!)

† በዚህ አብነትም በአድባራቱ ÷ በገዳማቱ ትልልቆቹ (ሊቃነ ጳጳሳት ፡ ጳጳሳት ፡ ኤጲስ ቆጶሳት÷ ቆሞሳት፡ አበምኔቶች፡ ገበዛዝቱ) አስቀድመው ያጥባሉ!

† ኋላ በፈንታው ካህናት ያጥቧቸዋል!



ተጋድሎ እና እረፍቱ

† በአረመኔ የሮም ገዢ ኔሮን ቄሣር በሴራ ክርስቲያኖችን ባስፈጀበት ዘመን አርሱም

'እንደ ጌታዬ ልሰቀል አይገባኝም'

በማለት የቁልቁሊት እንዲሰቅሉት ለምኖ

† ሐምሌ 5 ቀን 67 ዓ.ም በሰማዕትነት አርፏል።





ሐዋርያዉ ቅዱስ እንድርያስ

ዉልደት እና እድገቱ

- ቅዱሱ ሐዋርያ ተወልዶ ያደገው በቤተ ሳይዳ አካባቢ ነው
- የሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ ትንሽ ወንድም ነው።
- አባቱም ዮና ይባላል። ገና ከልጅነቱ ጀምሮ አሣ ማጥመድን ከትልቅ ወንድሙ ተምሯል።
- እድሜው ከፍ ባለ ጊዜ ኦሪትን ተምሮ የመጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስ ደቀ መዝሙር ሆኗል።
- የስሙ ትርጓሜ፡- እንድርያስ ማለት "ተባዕ" (ደፋር ፡ ብርቱ) ማለት ነው።

ድፍረት ሥጋዊ: ድፍረት መንፈሳዊ አለና!

ከአገልግሎት መጠሁት

† ጌታ ከጸም (ከገዳመ ቆረንቶስ) በተመለሰ ጊዜ እንድርያስ መንፈስ ቅዱስ አነሳስቶት ተከትሎታል። መጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስ " የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ እነሆ" ማለቱን ሰምቶ ቅዱስ እንድርያስ ጌታን ተከተለ።

† በዚህም የመጀመሪያው የክርስቶስ ደቀ መዝሙር ለመባል በቃ። (ዮሐ. 1:47)

† ሊቁ ማር ገላውዴዎስም እመቤታችንን ሲያመሰግናት:-

''ለመጀመሪያው ሐዋርያ ለእንድርያስ ላይማኖቱ ማርያም አንቺ ነሽ" (መልክዐ ስዕል)

ሀገረ ስብከቱ

† ቅዱሱ ሐዋርያ ስሉጥ (ፈጣን) አገልጋይ እንደ ነበርም ወንጌል ይነግረናል። (ዮሐ. 6:9, 12:22)

† ምንም ሳገረ ስብከቱ ልዳ ብትሆን ብዙ አሕጉረ ዓለምን ሰብኳል

† እኝህም በጥንት ስኩቴስ ወይም በርባሮስ (የዛሬይቱ ሩስያ) ቀጥሎም በቢታንያ፣ በገላትያ እና ሩማንያ በመዘዋወር አስተምሯል ::

† በቁስጥንጥንያም የመጀመሪያው ሊቀጳጳስ እንደነበር ይነገራል።

የቅዱስ እንድርያስ መጠሪያዎች

† የቤተሰብ ሐዋርያ

† የወጣቶች ሐዋርያ


† የአህዛብ ወዳጅ



ተጋድሎ እና እረፍቱ

† ታኅሣሥ 4 ቀን ቋጥሪስ በተባለች ቦታ የ'X' ቅርጽ ባለው መስቀል ተሰቅሎ በሰማዕትነት አርፏል።





ሐዋርያው ቅዱስ በርተሎሜዎስ

ዉልደት እና እድገቱ

በርተሎሜዎስ' የሚለውን ስም ያወጣለት ጌታችን ሲሆን

ትርጉሙም

'ተክሌችን የሚያጠጣ'

ማለት ነው::

ለአገልግሎት መጠሁት

በርተሎሜዎስ የግብርና ሥራውን ትቶ ፡ የጌታችን ኢየሱስ

ክርስቶስ ደቀ መዝሙር ሆኖ፡ ከዋለበት እየዋለ፡ ካደረበትም

እያደረ ምሥጢረ ወንጌልን ተምሯል።

ሀገሪ ስብከቱ



- ሳገረ ስብከቱም

  'እልዋህ'

  እና

  'አርማንያ' ናቸው

- በሀገራችን ኢትዮጵም መስበኩንና ሕዝቡን ያጠመቀባቸው ወንዞች ዛሬ ድረስ 'ብረት' እና 'ሎሚ' ውኃ ተብለው እንደሚጠሩም ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን ይናገራሉ።

ተጋድሎ እና እረፍቱ

† ቅዱስ በርተሎሜዎስ እያስተማረ ወደ ኢትዮድያም ደርሶ እንደ ነበር ይነገራል። በመጨረሻም 'ለሚስቶቻችን ንጽሕናን አስተምረሃል' በሚል ተከሶ:



† ንጉሥ አግሪዳ

† መስከረም 1 በሰቅ (ጸጉር) ጠቅልሎ: አሸዋ ሞልቶ: ባሕር ውስጥ ጥሎታል። በዚያውም ዐርፏል!

ስብሐት እእዛዘአብሔር!